# ያልታሰቡ የህክምና ክፍያዎችን በተመለከተ ያሉዎትመብቶች እና ጥበቃዎች

**የድንገተኛ የህክምና እንክብካቤ በሚያገኙበት ጊዜ ወይም ከአቅራቢ ኔትወርክ ውጭ በሆነ ሆስፒታል ሲታከሙ ወይም በተንቀሳቃሽ የቀዶ ህክምና ማዕከል በሚታከሙበት ጊዜ ካልታሰበ ክፍያ ወይም የማመጣጠኛ ክፍያ ጥበቃ ይደረግልዎታል።**

**“የማመጣጠኛ ክፍያ” (አንዳንድ ጊዜ “ያልታሰበ ክፍያ”) ተብሎ የሚጠራው ምንድን ነው?**
በዶክተር ወይም ሌላ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ በሚታዩበት ወቅት እንደ የጋራ ክፍያ፣ የጋራ መድን ዋስትና እና/ወይም ተቀናሽ ክፍያ እና የመሳሰሉ የተወሰኑ የኪስ ወጪዎችን ሊከፍሉ ይችላሉ። በጤና እቅድዎ ኔትወርክ ውስጥ ባልሆነ አቅራቢ የሚታዩ ከሆነ ወይም በጤና እቅድዎ ኔትወርክ ውስጥ ወዳልሆነ የጤና እንክብካቤ ተቋም የሚሄዱ ከሆነ ሌሎች ወጪዎችን መክፈል ሊኖሩብዎ ወይም ሙሉ ክፍያውን መክፈል ሊኖርብዎ ይችላል።
“ከኔትወርክ ውጭ” የሚለው ከጤና ዕቅድዎ ጋር ውል ያልተፈራረሙ አቅራቢዎች እና ተቋማትን ይገልጻል። ከኔትወርክ ውጭ ያሉ አቅራቢዎች እቅድዎ ሊከፍልልዎ በተስማማው ክፍያ እና ለአገልግሎቱ በሚከፈለው ሙሉ ክፍያ መካከል ያለውን ልዩነት እንዲያስከፍሉዎ ሊፈቀድላቸው ይችላል። ይህ “የማመጣጠኛ ክፍያ” ይባላል። ይህ የገንዘብ መጠን ለተመሳሳይ አገልግሎት ከኔትወርክ ውስጥ ካሉ ወጪዎች በላይ ሊሆን ይችላል እንዲሁም በአመታዊ የኪስ ወጪ ጣሪያዎ ውስጥ ላይካተት ይችላል።
“ያልታሰበ ክፍያ” ያልታሰበ የማመጣጠኛ ክፍያ ነው። ይህ በእርስዎ የጤና እንክብካቤ ላይ ማን እንደሚሳተፍ መቆጣጠር በማይችሉበት ወቅት ሊያጋጥም ይችላል- ለምሳሌ ድንገተኛ ህክምና ቢያስፈልግዎ ወይም በኔትወርክ ውስጥ ወደሚገኝ አቅራቢየህክምና ቦታ የሚያስኬድ ቀጠሮ ኖሮት ሳይታሰብ ከኔትወርክ ውጭ በሆነ የህክምና ባለሞያ ከታከሙ ነው።

**ለሚከተሉት ሁኔታዎች የማመጣጠኛ ክፍያ እንዳይከፍሉ ጥበቃ ይደረግልዎታል:**

**የድንገተኛ ህክምና አገልግሎቶች**
የድንገተኛ ህክምና ሁኔታ ካጋጠምዎት እና የድንገተኛ ህክምና አገልግሎቶችን ከኔትወርክ ውጭ በሆኑ አቅራቢ ወይም ተቋም ካገኙ አቅራቢው ወይም ተቋሙ ሊያስከፍልዎ የሚችለው ከፍተኛው ክፍያ የእቅድዎን የኔትወርክ ውስጥ የወጪ መጋራት ክፍያ ዋጋ (ለምሳሌ: የጋራ ክፍያዎች እና የጋራ መድን ዋስትና) ነው። ለእነዚህ የድንገተኛ ህክምና አገልግሎቶች የማመጣጠኛ ክፍያ ሊከፍሉ አይችሉም። የጽሁፍ ፍቃድ ካልሰጡ እና ከእነዚህ የድህረ ማገገም አገልግሎቶች በኋላ የማመጣጠኛ ክፍያ ያለመክፈል ያለዎትን ጥበቃ ካልተዉ በስተቀር ይህ በማገገም ሁኔታ ላይ ከሆኑ በኋላ ሊያገኙ የሚችሏቸው አገልግሎቶችን ያካትታል።

**በኔትወርክ ውስጥ ባለ ሆስፒታል ወይም ተንቀሳቃሽ የቀዶ ህክምና ማዕከል ውስጥ የሚቀርቡ የተወሰኑ አገልግሎቶች**
ከኔትወርክ ውስጥ ባለ ሆስፒታል ወይም ተንቀሳቃሽ የቀዶ ህክምና ማዕከል አገልግሎቶችን በሚያገኙበት ጊዜ የተወሰኑ አቅራቢዎች ከኔትወርክ ውጭ የሆኑ አቅራቢዎች ሊሆኑ ይችላሉ። በእነዚህ ሁኔታዎች ወቅት አቅራቢዎቹ ሊያስከፍሉዎት የሚችሉት ከፍተኛ ክፍያ የእቅድዎን የኔትወርክ ውስጥ ያለ የወጪ መጋራት መጠን ነው። ይህ ለድንገተኛ መድሀኒት፣ ማደንዘዣ፣ ፓቶሎጂ፣ ለራዲዮሎጂ፣ ለላብራቶሪ፣ ለጨቅላ ህጻናት ህክምና፣ ለረዳት ቀዶ ጥገና ሀኪም፣ ለየሆስፒታል ውስጥ አስተኝቶ ማከም ባለሙያ ወይም ለጽኑ ህሙማን ህክምና ክፍል ይሰራል። እነዚህ ህክምና አቅራቢዎች እርስዎን የማመጣጠኛ ክፍያ ማስከፈል የማይችሉ ከመሆኑም በተጨማሪ የማመጣጠኛ ክፍያ ያለመክፈል ጥበቃዎችዎን እንዲተዉ መጠየቅ አይችሉም።

ከእነዚህ የኔትወርክ ውስጥ ካሉ ተቋማት ሌሎች አገልግሎቶችን የሚያገኙ ከሆነ የኔትወርክ ውጭ ያሉ አቅራቢዎች እርስዎ የጽሁፍ ፍቃድ ካልሰጡ በስተቀር እና ያለዎትን መብቾች/ጥበቃዎችዎን ካልተዉ በስተቀር የማመጣጠኛ ክፍያ ሊያስከፍሉዎ አይችሉም።

**የማመጣጠኛ ክፍያ ያለመክፈል መብትዎን/ጥበቃዎችዎትን እንዲተዉ በፍጹም አይገደዱም። በተጨማሪም ከኔትወርክ ውጭ እንክብካቤ እንዲያገኙ አይገደዱም። በእቅድዎ ኔትወርክ ውስጥ የሚገኝ አቅራቢ ወይም ተቋም መምረጥ ይችላሉ።**

**በግዛት ቁጥጥር ለሚደረግባቸው የህክመና ዕቅዶች የሚቺጋን ግዛት የታካሚዎች ሕግ።**
የሚቺጋን ሕግ በግዛት ቁጥጥር ለሚደረግባቸው የጤና ወጪ እቅዶች ጥበቃዎችን ያደርጋል።
ለምሳሌ: ለታካሚዎች ድንገተኛ ያልሆነ እንክብካቤ የሚያቀርቡ ከኔትወርክ ውጭ ያሉ ህክምና አቅራቢዎች ለታካሚዎች የሚከተሉትን ጨምሮ የተወሰኑ መግለጫዎችን መስጠት አለባቸው:

- የጤና መድን ዋስትናዎ ከኔትወርክ ውጭ ያለ ህክምና አቅራቢው የሚያቀርብልዎትን ሁሉንም አገልግሎቶች ላይሸፍንልዎ እንደሚችል።
- የሚቀርቡት የአገልግሎቶች ወጪን በተመለከተ የቀና መንፈስ ግምት እንደሚሰጥ፤
- አገልግሎቶቹ በኔትወርክ ውስጥ ባለ ህክምና አቅራቢ እንዲሰጥዎ መጠየቅ እንደሚችሉ።

**በተጨማሪም የማመጣጠኛ ክፍያ እንዲከፈል የማይፈቀድ ከሆነ የሚከተሉት ጥበቃዎች ይደረጉልዎታል:**

- የመክፈል ኃላፊነትዎ የወጪውን ድርሻዎን ብቻ ነው (ለምሳሌ: የሚከፈሉ የጋራ ክፍያዎች፣ የጋራ መድን ዋስትናዎች ወይም ተቀናሽ ክፍያዎች የኔትወርክ ውስጥ ቢሆን የሚከፍሏቸው ተቀናሾች)። የጤና ወጪ እቅድዎ ክፍያውን ለኔትወርክ ውጭ ላሉ አቅራቢዎች እና ተቋማት በቀጥታ ይከፍልልዎታል።
- የጤና እቅድዎ በአጠቃላይ:
  - ለድንገተኛ ህክምና አገልግሎቶች በቅድሚያ ፍቃድ እንዲያገኙ (ቅድሚያ ፍቃድ) ሳይጠየቅ የድንገተኛ ህክምና አገልግሎቶችን መሸፈን አለበት።
  - ከኔትወርክ ውጭ በሆኑ ህክምና አቅራቢዎች የሚቀርቡ የድንገተኛ ህክምና አገልግሎቶችን መሸፈን አለበት።
  - ለኔትወርክ ውስጥ አቅራቢ ወይም ተቋም ለሚከፍለው ክፍያ በእርስዎ ለአቅራቢው ወይም ተቋሙ በሚከፍሉት ክፍያ (የወጪ መጋራት) ላይ መመስረት እና ይህን የገንዘብ መጠን በጥቅማ ጥቅሞች ማብራሪያዎ ላይ ማሳየት አለበት።
  - የትኛውምንም የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ለማግኘት ወይም ከኔትወርክ ውጭ ለሚያገኙት አገልግሎቶች እስከ ተቀናሽዎ እና የኪስ ክፍያዎ ጣሪያ ድረስ የሆነ የትኛውንም የገንዘብ መጠን መክፈል አለበት።

በስህተት ክፍያ እንድከፍል ተደርጌያለሁ ብለው ካመኑ እና በግዛት ቁጥጥር በሚደረግበት የጤና ወጪ እቅድ ስር ሽፋን ካልዎ ቅሬታዎን ለማስመዝገብ Michigan የመድን ዋስትና እና የፋይናንስ አገልግሎቶች መምሪያን በስልክ ቁጥር **877.999.6442** ሊያነጋግሩ ይችላሉ ወይም የDIFS ድረገጽን ሊጎበኙ ይችላሉ። የንግድ የመድን ዋስትና ሽፋን ካልዎ እና በስህተት እንድከፍል ተደርጌያለሁ ብለው ካመኑ ያልታሰበ ክፍያን እናስወግድ በሚል የተቋቋመውን የእርዳታ ዴስክ በስልክ ቁጥር **800.985.3059** ሊያነጋግሩ ይችላሉ።

በፌደራል ሕግ ስር ስለተሰጡዎ መብቶች በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት **cms.gov/nosurprises/Ending-Surprise-Medical-Bills** ን ይጎብኙ።

Michigan ህግ ስር ስለተሰጡዎ መብቶች በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት **michigan.gov/difs** ን ይጎብኙ እና ‘ያልታሰበ የህክምና ክፍያ’ (Surprise Medical Billing) የሚለውን ይጫኑ።

የተሟላ ዝርዝር ለማግኘት እባክዎ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ብሮሸር ይጠይቁ ወይም **corewellhealth.org/policies** ን ይጎብኙ

Corewell Health © 10.2023